# <u>የአራተኛ ክፍል ትምህርት ሰሌዳ</u>

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ከ0-9 ካሉ ቁጥሮች እያንዳንዱን አንድ ግዜ ብቻ ተጠቀም። ከዚያም እንዴት ትልቁን ቁጥር ማግኘት እንደ ሚቻል ግለጽ። እንዲሁም እንዴት ትንሹን ቁጥር ማግኘት እንደ ሚቻል ግለጽ።. | ከቀደምት አመሪካውያን (Native Americans) ወይ ከቨንጂንያ ሰፋሪዎች (Virginia settlers) እይታ አንጻፍ ግጥም ጻፍ። | ስለ ተለያዩ የደመና ዓይነቶች (Cirrus, Stratus, Cumulus, Cumulo-Nimbus) መዝሙር ጻፍ ከዛም ለአንድ ሰው ዘምርለት። | ለ30 ደቂቃ ካነቡብክ በኋላ ስላነቡብከው ጻፍ። በመጽሓፉ ውስጥ ያሉ ገጸ ባህርያት ምን ያለመግባባቶች ነው ያገጠማቸው? ለፈታኝ ሆኔታዎች ምን ምላሽ ሰጡ? | መጀምርያ ግዜ ወስዳቹ ሰውነታቹን አፍታቱ። ከዛም ፑሽ-አፕ መስራት፣ ቤት ውስጥ ዱብ ዱብ በል፣ በጀርባህ ተኝተህ ከወገብህ መነሳት፣ (ከትልቅ ሰው ፍቃድ ጠይቀህ) ከቤት ውጭ በእግር መዘዋወር የመሳሰሉትን ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን አድርግ። |
| | ሁለት ዳይስ አንከባልል ከዛም ብዜቱን ለማወቅ ቁጥሩን አባዛው። ብዜቱን መዝግበው። 25 ግዜ እንደዚህ አድርግ። ውጤቶቹን ተጠቅመህ የባር ግራፍ ወይም አሞሌ ግራፍ ስራ። ምን አስተዋልክ? | ለዘመድ ለጓደኛ ለወይ ጎረቤት ቃለ መጠይቅ አድርግ፣ ከዛም በዛ ሰው ህይወት የተከሰቱ ወሳኝ ክንውኖችን የሚያሳይ የግዜ ሰሌዳ ስራ። | በዛሬ ዕለት ቤተሰብህ ውሃ የተጠቀመበት መገድ የሚገልጽ ዝርዝር ጻፍ። ነገ እንዴት ውሃ መቆጠብ እንደ ምትችል አስብ። | አንድ በግል የታተመ መጽሓፍ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ አንብብ። ሁለት ገጸ ባህርያትን እያነጻጻርክ ጻፍ። | የራስን ምስል መሳል። በመስታወት እያየህ የራስህ ምስል ሳል። በተቻለህ መጠን የምታያቸውን እያንዳንዱን ዝርዝር ገጽታ አካትት። . |
| | . በየደቂቃው አራት ግዜ ዝለል። ከዛም የግብዓትና ውጤት ሰንጠረዥ (input-output table) ሰርተህ ለዛ የሚሆን ሕግ ጻፍ። በ10 ደቂቃ ውስጥ ስንት ግዜ መዝለል ትችላለህ? በ22 እና በ 45 ደቂቃዎች ውስጥስ? | ቤት ውስጥ አግዝ፦ ክፍልህን አጽዳ፣ የተጠበ ልብስ አጣጥፍ፣ ሳህኖች እጠብ ወይም ቤት ጥረግ/ቫክዩም አድርግ። | ሜትሮሎጂስት ለመሆን ሞክር ስለ የዛሬ የሙቀት መጠን፣ ንፋስ፣ ዝናብ እንዲሁም ደመና ባለ አንድ አንቀጽ ሪፖርት ጻፍ። ከሪፖርቱ ጋር የሚሄድ ስእል ሳል። | መጽሓፍ አስተዋውቅ! ለጓደኛህ አንድ መጽሓፍ እንዲያነብ ሓሳብ አቅርብለት፣ ሌላን ሰው ምን መጽሓፍ እንድታነብ እንደ ሚመክርህ ጠይቅ። ምክንያቱን መግለጽ አትርሳ ! | የምትወደውን መዝሙር እየዘመርክ በግሮችህ ጣት ቁም። |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቤት ውስጥ 5 ድርድር (array) እቃዎች ፈልግ። በየትኛው ዕቃ ተጠቅመህ ድርድሩን (array) እንዳሰመርክው ጻፍ። ሁለት የብዜት ቀመር ጻፍ ከዛም የሰራህውን መልስ አሳይ። | ከሳይንስ ወይም ከማሕበረሰብ ጥናት አንድ ምዕራፍ መርጠህ ግጥም ጻፍ (ለምሳሌ ዕምቅ ሃይልና ግጭት፣ Colonial Virginia) | ሙከራ አካሂድ። መልስ ልታገኝበት የምትችል ጥያቄ በመጠየቅ ጀምር፣ ለምሳሌ "በረዶ በምን ያህል ግዜ ውስጥ ይቀልጣል?" | ለረጅም ግዜ ላላገኘህው ሰብ ደብዳቤ ጻፍ። በህይወትህ ውስጥ እየሆነ ስላለው ነገር ንገራቸው ስለ እነሱም ጠይቅ። | በአንድ ደቂቃ ውስጥ በግራ እግርህ ምን ያህል ግዜ መዝለል ትችላለህ? በቀኝ እግርህስ? የዘለልከው ቁጥር በ <, >, ወይም = ተጠቅመህ አወዳድረው። ልዩነቱ ምን ያህል ነው? |
| | በቀኑ ውስጥ አንድ ነገር ማድረግ የጀመርክበትንና ያቆምክበትን ሰዓት መዝግብ። እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ስንት ግዜ ፈጀብህ። | ትምርት ቤትህ ውስጥ ለሚሰራ ሰው የምስጋና ደብዳቤ ጻፍ። ስለ እነሱ የምታደንቀውን ነገር፣ ት/ቤት ውስጥ ስለ ሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ንገራቸው። ስለ ሁሉ ስራቸው አምሰግናቸው። | Epic ተጠቅመህ ስለ ፕላኔቶች ተማር! እያንዳንዱ ፕላኔት ከፀሃይ ባላቸው ርቀት መሰረት በድያግራም አሳይ። ስለ እያንዳንዱ ፕላኔት ልዩ ገጽታ ጻፍ። | ድምጽ እየለዋወጥክ ተረት በምትተርትበት ድምጽ መጽሓፍ ማንበብ ተለማመድ። ስታነብ ወላህጅ በሞባይሉ ከቀዳህ የተቀዳውን ቪድዮ ለዘመድ ወይ ለጓደኛ ላክለት! | እጅህንና እግርህን ከመሬት ሳታነሳ እጅህን ወደ ኋላ አድርገህ ቤት ውስጥ 3 ግዜ ወደ ፊት ሂድ። ከዛም 3 ግዜ ወደ ኋላ ተመለስ። |
| | በቅርቡ ያነበብከው ታሪክ ውስጥ ያሉትን ገጸ ባህርያት ተጠቅመህ እስከ 999,99 የመደመር ወይ የመቀነስ የሂሳብ ጥያቄ ፍጠር። | በማሕበረሰብህ ውስጥ የሚሰጥ አገልግሎት ስለ ተጠቀምክበት ግዜ የሚገልጽ አንድ አንቀጽ ጻፍ። | ውሃ ውስጥ የትኞቹ ዕቃዎች እንደ ሚንሳፈፉ የትኞቹ እንደ ሚሰምጡ ለመለየት ሙከራ አካሂድ። ቀደም ተከተሉን መዝግብ ግኝትን ጻፍ። | አንድ ደስ የሚል የንባብ ቦታ ፍጠር። ለአንድ አሻንጉሊት መጽሓፍ አንብብ፣ ስታነብ ምን እንደ ተሰማህ ለአሻንጉሊቱ ንገረው። | ፍቃድ ጠይቀህ ለራስህ ለጓደኛህ ወይም ለቤተሰብህ አባል ጤነኛ መክሰስ ስራ። አሰራሩህን ፅፈህ ለክፍልህ ተማሪዎች ንገራቸው። |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተጠቅመህ መጽሓፍ ጻፍ ወይ በስእል ግለጽ። | ከታሪክ ስለ ምታደንቀው አንድ ሰብ አስብ። ለዛ ሰው ክብር ስለ ሚከበር በዓል ጻፍቀቀለ | የውሃ ተፋሰሶችን ስለ መጠበቅ አንድ አሳማኝ አንቀጽ ጻፍ። ይህንን ሓረግ አብራራ፦“we all live downstream” | ስለ ምትወደው የቀለም ዓይነት ግጥም ጻፍ። ግምኡ ላይ ያንን ቀለም የሚያስታውሱህ ዕቃዎች፣ በታዎች ወይ ስሜቶች አካትት። | ወደ ውጪ ተመክተህ የምታየውን ነገር ለመሳል ሞክር። ፊት ለፊት መሃል እና ከጀርባ ያሉትን አካትት። |
| | ከ1-9 ባሉት ቁጥሮች ቢያንስ እያንዳንዱን አንድ ግዜ በመጠቀም ሁለት ባለ 4-ዲጂት ተደማሪ ቁጥሮችን ተጠቅመህ ወደ 10,000 የሚጠጋ ድምር ለማግኘት ሞክር። [ ] [ ] [ ] [ ] + [ ] [ ] [ ] [ ] | የጊዜ ጉዞ (Time Travel): በታሪክ የጊዜ ሰሌዳ ወደ ኋላ መመለስ ብትችል የትኛውን ጊዜ መጎብኘት ትፈልጋለህ? ምን ማድረግስ ትፈልጋለህ? ማንን ማግኘት ትፈልጋለህ? ስዕል ሳል፤ ታሪክ ፃፍ ወይም ለቤተሰብ አባልህ ንገር። | የጊዜ ጉዞ: አዳዲስ ፈጠራ የሚፈጥሩ ሰዎች ወደ ፊት አዲስ መሳርያዎችን ተጠቅመው ሊፈትዋቸው የሚችሉ ዛሬ ሰዎች የሚጋጥማቸው ችሮች ምንድን ናቸው? የመሳርያውን ስእል ስለህ ችግሩን እንዴት እንደ ሚፈታው አስረዳ። | ከመጽሓፍ ውስጥ አንድ ስሜቱን የሚገልጽ ገጸ ባህርይ ምረጥ። እንዴት ነው የተሰማው? ይህ ስሜት እንዳላቸው ከመጽሓፉ ውስጥ የሚያሳይ 2 ዝርዝር ነገሮች ጻፍ። | በአንድ ሙዚቃ ዳንስ ፍጠር ከዛም ቤት ውስጥ ላለ ሰው ደንስለት። |
| | ከ9 ጀምረህ የመጀመርያዎቹን የ9 ብዜት የሆኑትን 10 ቁጥሮች ዘርዝር። በዝርዝሩ ውስጥ በ10ኛ ቦታ ባሉት አሃዞች ምን ዓይነት አሰዳድር (patterns) አስተዋልክ? በመጀምርያው ረድፍ ባሉ ቁጥሮች ምን ዓይነት አሰዳድር (patterns) አስተዋልክ? ስእሎችን ቃላትን ወይም ቀመር ተጠቅመህ ያስተዋልከውን አሰዳድር ግለጽ። | Clever ላይ ወደ PebbleGo ግባ። መጎብኘት ስለ ምትፈልገው ስቴት፣ አከባቢ ወይም ሃገር አንብብ። ስለ ቦታው አስፈላጊ ዝርዝሮችን ጻፍ። | የውቅያኖስ ወለል ምን እንደሚመስል በስእል ለማሳየት ሞክር። ውቅያኖስ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳትን መሳል አትርሳ እንዲሁም የውቅያኖስ ወለል ምን ሊመሲል እንደሚችል ሃሳብን ጻፍ። | Clever ላይ ወደ PebbleGo ግባ። ስለ አንድ አዲስ ሰው የህይወት ታሪክ አንብብ። ዋና ዋና ሓሳቦችንናን ስለዛ ሰው አስፈላጊ ዝርዝሮች ማስታወሻ ጻፍ። | አሁን ደግሞ እንቀሳቀስ! ለ1 ደቂቃ ዝለል (Do jumping jacks)። እያንዳንዱን ዝላይ በ2 አባዛው። ስታቆም ያቆምክበትን ቁጥር መዝግብ። በድጋሚ ዝለል እያንዳንዱን ዝላይ በ3 አባዛው። ያገኛሃቸውን ቁጥሮች ደምር ቀንስ። |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | .<br>ከ1-9 ባሉት ቁጥሮች ቢያንስ እያንዳንዱን አንድ ግዜ በመጠቀም በእያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ ወደ 1,000 የሚጠጋ ብዜት ከመጻፍ ሞክር።<br>□ □ X □ □ | የቨርጂንያን ክልሎች ካርታ ሳል። ክልሎቹን፣ ወንዞቹን እና የውሃ ክፍሎቹን፣ ተራራዎቹን ለይተህ አሳይ። ካርታህን ተጠቅመህ ለአንድ የቤተሰብ አባል ስለ አምስቱ ክልሎች ንገር። | በአንዱ የቨርጂንያ ክልል ውስጥ ከቤት ውጪ እየተዘዋወርክ እንደሆነ አድርገህ አስብ። በጉዞህ ላይ ምን ማድረግ ትፈልጋለህ? ስለ ጉዞህ የሚገልጽ አንድ ኣንቀጽ ጻፍ። | Clever ላይ ወደ Visit World Book ግባ። አሳተፊ የሆነውን ካርታ ተጠቅመህ ከዚህ ቀደም ሄደህበት የማታውቀውን ከተማ ጎብኝ። ዋና ዋና ሐሳቦችንናን ስለ ቦታው አስፈላጊ ዝርዝሮች ማስታወሻ ጻፍ። | ከወላጅ/ጠባቂ/ ወንድም ወይ እህት/ጓደኛ ጋር ለአስር ደቂቃ በካልሲ ኳስ ሰርታቹ ቅብብሎሽ ተጫወቱ። |